| | |
|---|---|
| አንደኛ ዓመት ቁጥር 1<br>1[st] Year No-1 | ሐረር መጋቢት4 ቀን 1988<br>HARAR March 13 1996 |

# የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

## ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

## HARAR NEGARI GAZETA

## HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ 1.00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት<br>ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 1/ 1988

የሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ .......................................................................... ገጽ1

## አዋጅ ቁጥር 1/1988

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

## የሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 52 መሠረት የክልል ምክር ቤቶች በየክልላቸው ሥልጣን ሥር በሆኑ ጉዳዮች ላይ የክልላቸው የህግ አውጪ አካላት በመሆናቸው፣

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በመሥራች ጉባኤው ተቋቁሞና የክልሉንም ህገ-መንግሥት አጽድቆ ሥራውን በይፋ የጀመረ በመሆኑ፣ የክልሉ ምክር ቤትና የክልሉ ምክር ቤት አካል የሆነው የሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ የክልሉን ሕዝብ ሕይወት ለመለወጥ በክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 20 23 ና 21 በተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት የሚያወጧቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎች በህግና ደንብ መልክ ተቀርጸው የሚታወጁበትን ክልላዊ የህግ ጋዜጣ ማቋቋም በማስፈለጉ፣

በሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግሥት አንቀጽ 27 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ፣

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1/1988" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. "ሕገ-መንግሥት" ማለት ጳጉሜ6ቀን 1987ዓ.ምየሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክርቤት ያጸደቀው ሕገ-መንግሥት ነው።

2. "ክልል" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልል ነው።

3. "ምክር ቤት" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት ነው።

4. "የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነው።

3. መቋቋም

በሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት የበላይ ጠባቂነት የሚወጣ የሐረር ነጋሪ ጋዜጣ (ከዚህ በኋላ "ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ") እየተባለ የሚጠራ የሕግ ጋዜጣ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

4. በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ሕጎችን የማውጣት ሥልጣን ያላቸው አካላት

በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማውጣት የሚችሉ አካላት ከዚህ በታች የተመለከቱት ናቸው።

ሀ. የክልሉ ምክር ቤት

ለ. የሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ እና

ሐ. የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣን ሲሰጠው የክልሉ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ናቸው።

5. ስለተፈጻሚነት

ማንኛውም የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት እና በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ማናቸውም በተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ የሚታወጁትን ወይም የሚወጡትን ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን የመቀበልና የማክበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

## ክፍል ሁለት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

6. ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ስለሚታተምበት ቋንቋ

የሐረር ነጋሪ ጋዜጣ በሐረሪ፣ በኦሮምኛና በአማርኛ ቋንቋዎች የሚታተም ይሆናል። በሐረሪና በኦሮምኛ ቋንቋዎች መካከል የይዘት ልዩነት በሚከሰትበት ጊዜ የአማርኛ ቅጅ ተቀባይነት ይኖረዋል። እንዲሁም የሐረሪና የኦሮምኛ ቋንቋዎች በአንድ በኩል ሆነው ከአማርኛው ትርጉም ጋር ልዩነት ቢኖራቸው የሐረሪና የኦሮምኛው ትርጉም ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

6. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር መጋቢት 04 ቀን 1988

አብዱላሂ ኢድሪስ

የሐረሪ ሕ/ብ/ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዚዳንት